# በአማራ ክልል በድሮን ጥቃት በርካታ ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸውን ኢሰመኮ ገለጸ

By ፍርቱና ወልደአብ - 31/10/2023

ማክሰኞ ጥቅምት 20 ቀን 2016 (አዲስ ማለዳ) በአማራ ክልል እየተካሄደ ያለው የትጥቅ ግጭት በአንዳንድ አካባቢዎች በከባድ መሣሪያ እና አልፎ አልፎ በአየር/ድሮን ድብደባ ጭምር የታገዘ ነው ሲል የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ገልጿል።

ኮሚሽኑ በአማራ ክልል ለወራት የቀጠው የትጥቅ ግጭት ዐውድ እና አሉታዊ የሰብዓዊ አንደምታውን አስመልክቶ ትናንት ጥቅምት 19/2016 ባወጣው የምርመራ ሪፖርት፤ በትጥቅ ግጭቱ በሲቪል ሰዎች ላይ ሞት እና የአካል ጉዳት መድረሱን አስታውቋል።

ኮሚሽኑ በክልሉ ብዙ ወረዳዎች ውስጥ የትጥቅ ግጭት መከሰቱን የገለጸ ሲሆን፣ ከሐምሌ ወር 2015 ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ የአማራ ክልል ኹሉም ዞኖች በተለያየ ደረጃና ጊዜ የትጥቅ ግጭት ተካሂዶባቸዋል ብሏል።

በተጨማሪም “እነዚህ አካባቢዎች ወይም ወረዳዎች በአንድ ወቅት በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች፣ በሌላ ወቅት በታጣቂው ቡድን (በተለምዶ ፋኖ በመባል የሚታወቀው) ቁጥጥር ሥር ውለዋል” ያለው ኮሚሽኑ፤ የትጥቅ ግጭቱ በአንዳንድ አካባቢዎች በከባድ መሣሪያ እና አልፎ አልፎ በአየር/ድሮን ድብደባ ጭምር የታገዘ እንደሆነ አስታውቋል፡፡

ለአብነትም በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በረኸት ወረዳ፣ መጥተህ ብላ ከተማ ጥቅምት 5/2016 በተፈጸመ የድሮን ጥቃት የአንድ ዓመት ከሰባት ወር ሕፃንን ጨምሮ በርካታ ሲቪል ሰዎች እንደተገደሉ እና የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ገልጿል፡፡

በተመሳሳይም በደብረ ማርቆስ ከተማ ጥቅምት 8/2016 በተፈጸመ የድሮን ጥቃት ቢያንስ 8 ሲቪል ሰዎች እንደተገደሉ፣ እንዲሁም በደንበጫ ከተማ ጥቅምት 3/2016 በከባድ መሣሪያ ድብደባ ምክንያት ሲቪል ሰዎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳት መድረሱን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የአካባቢው ነዋሪዎችና የዐይን ምስክሮች ጠቅሶ ጠቁሟል፡፡

በዚህም ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቃትን አልያም ግጭትን በመሸሽ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ ከቀያቸው ተፈናቅለው በአሳሳቢ ኹኔታ ላይ እንደሚገኙ አመላክቷል፡፡

ከ3 ሺሕ በላይ የሚሆኑት የምንጃር ወረዳ የአውራ ጎዳና ጎጥ ነዋሪዎችም ከመስከረም 6/2016 ጀምሮ ከቀያቸው ተፈናቅለው አሞራ ቤቴ ቀበሌ በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤትና ክፍት ሜዳ ላይ ተጠልለው እንደሚገኙ የጠቆመው ኮሚሽኑ፤ ሌሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ ሰዎች መተሀራና አዋሽን ጨምሮ ወደ ሌሎች አካባቢዎች መፈናቀላቸው ገልጿል፡፡

እንዲሁም ግጭቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የመንግሥት የጸጥታ አካላት በመንገድ ላይ ወይም ቤት ለቤት ፍተሻ በማድረግ ከያዟቸው በርካታ ሲቪል ሰዎች ውስጥ “ፋኖን ትደግፋላችሁ፣ ለፋኖ መረጃ ትሰጣላችሁ፣ መሣሪያ አምጡ፣ የተኩስ ድምጽ ስለተሰማበት አቅጣጫ መረጃ ስጡ” በሚልና ይህንን በመሰሉ ምክንያቶች ከሕግ ውጭ የሆኑ ግድያዎች መፈጸማቸውን የሚያሳዩ ተዓማኒ መረጃዎች ለኮሚሽኑ እንደደረሱት አመላክቷል፡፡

እንደማሳያም “በባሕር ዳር ከተማ፣ ሰባታሚት አካባቢ መስከረም 29 እና 30/2016 ሦስት ወንድማማቾችን ጨምሮ በርካታ ሲቪል ሰዎች፣ በሰሜን ጎጃም ዞን፣ አዴት ከተማ መስከረም 29/2016 ፍልሰታ ደብረ ማሪያም የሚኖሩ 12 የአብነት ተማሪዎችን ጨምሮ ሌሎች ሲቪል ሰዎች፣ በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ አማኑኤል ከተማ ጥቅምት 3/2016 ቢያንስ 8 ሲቪል ሰዎች በቤት ለቤት ፍተሻ መገደላቸውን” ተረድቻለሁ ሲል ኮሚሾኑ ገልጿል፡፡

እንዲሁም በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ ጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ፣ ግንደወይን ከተማ ሞጣ በር ተብሎ በሚጠራ አካባቢ መስከረም 18/2016 አንድ በጥይት የቆሰለን ግለሰብ እናቱና እህቱ በባጃጅ አሳፍረው ወደ ሕክምና ተቋም በመውሰድ ላይ እያሉ፤ የመንግሥት የጸጥታ አካላት ባጃጁን አስቁመው ኹሉንም ተሳፋሪዎች ካስወረዱ በኋላ “የቆሰለው እኛን ሲዋጋ ነው” በሚል ምክንያት የባጃጅ አሽከርካሪውን ጨምሮ አራቱን ሰዎች በጥይት መግደላቸውን ኮሚሽኑ ከነዋሪዎች ማረጋገጡን አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል በየደረጃው የሚገኙ ሲቪል የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች፣ ግድያዎችና እገታዎች በታጠቁ ኃይሎች ተፈጽመዋል ያለው ኮሚሽኑ፤ እንደምሳሌም መስከረም 28/2016 የአማራ ክልል ምክር ቤት የሕግ፣ ፍትሕና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢን ጨምሮ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከባሕር ዳር ወደ ደብረ ታቦር ሲሄዱ አለምበር ከተማ አካባቢ በታጣቂዎች መገደላቸውን አስታውሷል፡፡

በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት በመሰንዘር ታራሚዎችና ተጠርጣሪዎች እንዲያመልጡ መደረጉንም ገልጿል፡፡

ኮሚሽኑ ባደረገው ክትትል በተለይም ከመንግሥት ተቋማት ጭምር በሚደርሱት መረጃዎች መሠረት በግጭቱ ዐውድ የሚፈጸሙ የአስገድዶ መድፈር ድርጊቶች በጣም አሳሳቢ መሆናቸውን የገለጸ ሲሆን፤ በአፋጣኝ ተገቢው ምርመራ ተደረጎ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚገባም አሳስቧል፡፡

የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት በተለያዩ የጤና ተቋማት መድረስ የቻሉትን ተጎጂዎች ቁጥር ብቻ መሠረት በማድረግ፣ ከሐምሌ ወር 2015 ጀምሮ ይህ መግለጫ እስከወጣበት ትናንት ጥቅምት 19/2016 ድረስ ቢያንስ 200 የአስገድዶ መድፈር ተጎጂዎች በጤና ተቋማት ተመዝግበዋል ያለው ኢሰመኮ፤ ከተጎጂዎች መካከልም የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ሴቶች እና የጤና ባለሞያ ሴቶች ጭምር እንደሚገኙበት ገልጿል፡፡

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ፤ ግጭቱን በዘላቂነት ለመፍታት ለኹሉም ሰላማዊ አማራጮች አሁንም ቅድሚያ መስጠትን ጨምሮ፤ ተፋላሚ ወገኖች ሲቪል ሰዎችንና ንብረቶችን፣ የሕዝብ አገልግሎቶችን እና መሠረተ ልማቶችን በማናቸውም ኹኔታ ዒላማ እንዳያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

እንዲሁም በቁጥጥር ሥር የዋሉ የታጠቁ ኃይሎች አባላትና ሌሎች ተጠርጣሪዎችም ኹኔታ በሕጋዊ አግባብ ብቻ እንዲስተናገድ፤ በተለይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እና ከሕግ ውጭ የተፈጸመ ግድያ በአስቸኳይ በማጣራት ተጠያቂነት እንዲረጋገጥና የማኅበራዊ አገልግሎቶች በተቻለ ፍጥነት እንዲቀጥል ሲሉ አሳሰዋል፡፡

---

---

**ፍርቱና ወልደአብ**


ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የተም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች፡፡

ይከታተሉን